AABE
Accounting and Auditing Board of Ethiopia
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድ

ኢኮኖሚ

ከኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር በ15 ቀን የሚታተም

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር፤ የሚሰራችው ሥራዎች

ሰሚራ በርሀ

የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና አዲት ቦርድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 የተቋቋመ እና ተጠሪነቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር የሆነ መንግሥታዊ ተቋም ነው። ይህ ቦርድ ከተለያዩ አካላት በተወጣጡ 12 የቦርድ አባላት የሚመራ ተቋም ሲሆን ቦርዱ ወደ ሥራ ከገባ ከስምንት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል።

በዛሬው ዕትማችን የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና አዲት ቦርዱን ማቋቋም የስፈለገበት ምክንያት፣ የቦርዱ ዓላማ፣ ሥልጣን እና ተግባር ምን እንደሚመስል የቦርዱ ዋና ዳይሬክተር ከሆኑት ወይዘሮ ሂክመት አብደላ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናል። የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና አዲት ቦርድ በአሁን ሰዓት ኃላፊነት ወስዶ ከሚሰራቸው ሥራዎች መካከል ሒሳብ እና ለአዲት ባለሙያዎች ፍቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ መሰረዝ፣ በባለሙያዎች ላይ የስትትል እና ቁጥጥር ሥራ መሥራት እንዲ ነው።

ቦርዱ ከመቋቋሙ በፊት በሀገራችን ሒሳብ እና ለአዲት ባለሙያዎች ፍቃድ በማን እንደሚሰጥ እና ባለሙያዎቹ በምን መልኩ ሥራዎቻቸውን እንደሚያከናውኑ ስንመልከት፣ ከአፄ ኃይለሥላሴ ሥርዓተ መንግሥት ጊዜ ጀምሮ ሲሰጅም ዓመታት የሒሳብ ሙያ እንደ የሃንዮሽ ሥራ ሆኖ በተደራቢ የሚከናወን ነበር። ለብዙ ዓመታትም ሒሳብ እና ለአዲት ባለሙያዎች ፍቃድ የሚሰጠው በፈዴራል እና በክልል ዋና አዲተር መ/ቤት ነበር። ይሁን እንጂ የፈዴራል እና የክልል ዋና አዲተር መ/ቤት ተልዕኮ የመንግሥት ተቋማትን አዲት በማድረግ የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት ማስያዝ እንጂ ለባለሙያዎች ፍቃድ መስጠት እና መቆጣጠር አልነበረም። ፍቃድ ከመስጠትም ባሻገር በባለሙያዎች ላይ የሚያደርገው የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ በሚፈለገው ደረጃ አልነበረም ፤ የቁጥጥር ሥርዓት ነበረው ወይ የሚለውም ከተያቴ ውስጥ የሚገባ ነበር።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሪፖርት አቅራቢ አካላት የፋይናንስ ሪፖርታቸውን በአላተርሞኛው አማካኝነት አዘጋጅተው ወደሌላ ተቋም በሚሄዱበት ጊዜ የፋይናንስ ሪፖርት በምን መልኩ አዘጋጅተው ማቅረብ እንዳለባቸው የሚያሳይ የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በባለሙያዎች መካከል አለመተማመን ነበር የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ውጥነት ለማስያዝ አስቸጋሪ ነበር። በመሆኑም ይህንን ባለቤት ያልነበረውን እና ትልቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ሥራ በኃላፊነት ወስዶ ለመሥራት እንዲቻል የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ በሥራ ላይ ይገኛል።

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ ቦርዱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 ተቋቁሞ በአዋጅ እና በደንቡ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሪትን ያከናውናል። ስለሆነም ቦርዱ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች ላይ ተግባሪዊ የሚደረግ የተሟላ፣ ግልጽ እና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ ውጥ የሆነ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ሕግ መኖሩ ያልተማከለ የነበረውን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ በማማከል ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ለማጎልበት፣ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ምዕራፎች ለመደገፍ፣ የፋይናንስ ቀውስ እና የድርጅቶችን የውድቀት ሥጋት እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን አሉታዊ የኢኮኖሚ ውጤቶች ለመቀነስ ከድርጅቶች የሚገኘውን የፋይናንስ መረጃ አቅርቦት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል በእጅጉ የሚያማዝ ነው።

ቦርዱ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ለሚያማሉ የሒሳብ እና የአዲት ባለሙያዎች ፍቃድ ይሰጣል። ፍቃድ ከሰጠ በኋላም ባለሙያዎቹ

ወይዘሮ ሂክመት አብደላ፡

የሚያከናውኑት ሥራ በሚፈለገው ደረጃ መሆኑን እና የሙያ ሥነ-ምግባርን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል። የሒሳብ ሙያ ከሌሎች ሙያዎች ለየት የሚያደርገው ከዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ጋር የሚያስተሳስር መሆኑ ነው። ይህም ፍቃድ የተሰጣቸው የሒሳብ እና የአዲት ባለሙያዎች የሚያዘጋጇት የፋይናንስ ሪፖርት ጥራቱ ተረጋግጦ ለተለያየ አካላት የሚቀርቡ እና ለተለያዩ ጥቅሞች የሚውሉ በመሆናቸው ነው። አንድ የፋይናንስ ሪፖርት ሲዘጋጅ ቀድሞ የነበረው አሰባሰብ ሥርዓቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሀገር ውስጥ ገቢ የሚገኝ ማብርን በተገቢው ሁኔታ ለመሰብሰብ የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ጥኮች ብድር የሚሰጡት የፋይናንስ ሪፖርትን እንደመስፈርት ተጠቅመው ነው። እንዲሁም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች/ኢንቨስተሮች መዋለ-ንዋያቸውን ለማፍሰስ የድርጅቶችን የፋይናንስ ሪፖርት መሠረት በማድረግ በመሆኑ ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ነው።

ቦርዱ እንደተቋቋመ የመጀመሪያ ሥራው ያደረገው በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሥርዓተ-ትምህርታቸው እንዲያካትቱና ባለሙያን እንዲያፈሩ፤ ቦርዱ ያዘጋጀውን መስፈርት የሚያማሉ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ወጥነት ባለው መልኩ እንዲተገበሩ በርካታ የግንዛቤ መስጫ መድረኮች ተከናውነዋል። በመሆኑም የሪፖርት አቅራቢ አካላት በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች(International Financial Reporting Standards, IFRS) ዓመታዊ የፋይናንስ መግለጫ ሪፖርታቸውን እንዲያዘጋጁ ይፉ አድርጓል።

እንዲሁም የሪፖርት አቅራቢ አካላት በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች (IFRS) መሠረት የሒሳብ መግለጫ ሲዘጋጅም አራት መሰረታዊ መስፈርቶችን መያዝ አለበት። እነዚህም የሒሳብ አመዘጋገብ (Recognition)፤ የመለኪያ (Measurement)፤ የአቀራረብ (Presentation) እና የማሳወቅ (Disclosure) መስፈርቶች ናቸው።

ቦርዱ የተቋቋመበት ዓላማ አምስት ሲሆኑ እነዚህም ቦሪፖርት አቅራቢ አካላት/ድርጅቶች የሚቀርቡ የፋይናንስ እና ተያያዥነት ያላቸውን ሪፖርቶች አዘገጃጀት እና አቀራረብ ጥራት ማስጠበቅ፤ የአዲተሮች እና የሂሳብ ባለሙያዎችን የሙያ ደረጃ ማስጠበቅ፤ የሒሳብ አያያዝ እና የአዲት አገልግሎት ጥራት ማስጠበቅ፤ የሒሳብ ሙያ የሕዝብ ጥቅምን ማስጠበቁን ማረጋገጥ እና የሒሳብና የአዲት ባለሙያዎችን የሙያ ነፃነት ማስከበር ናቸው።

ቦርዱ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት በአዋጅ እና በደንቡ በርካታ ሥልጣን እና ተግባራት የተሰጡት ሲሆን ከሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ ከሒሳብ/ከአዲት ባለሙያዎች እና ከሒሳብ ሙያ ማኅበራት ጋር የሚገናኙ ናቸው።

ከሪፖርት አቅራቢ አካላት እና ከፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች ጋር በተያያዘ ቦርዱ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች እና የአዲት ሥራዎችን በተመለከተ ደረጃዎችን እና የአፈጻጸም መመሪያዎችን የማውጣት እንዲሁም መከበራቸውን የማረጋገጥ፤ ሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት የማውጣት፤ የሒሳብ መግለጫዎችን የመመዝገብ፤ የፋይናንስ ሪፖርት እና የአዲት ደረጃዎችን ለማስጠበቅ የሒሳብ መግለጫዎችን የመመርመር፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሪፖርት አቅራቢ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ፤ እና ከፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ፣ ከሒሳብ አያያዝ እና የአዲት ሥራ እንዲሁም ከድርጅቶች አመራር (Corporate Governance) ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በሚመለከት መንግሥትን የማማከር ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ቦርዱ የሪፖርት አቅራቢ አካላትን በሚመለከት በርካታ ሥልጣን እና ተግባር እንደተሰጠው ከፍ ብሎ ተገልጿል። ነገር ግን ሪፖርት አቅራቢ አካል የሚባለው ማን ነው? ምን ዓይነት ድርጅቶችን/ተቋማትን ያካትታል የሚለውን እንመልከት።

ሪፖርት አቅራቢ አካል ማለት የመንግሥት መ/ቤቶችን እና ጥቃቅን ድርጅቶችን ሳይጨምር ማንኛውም በሕግ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ያለበት አካል ነው። በዚህም መሠረት በትርጉሙ ውስጥ እንዲይከተቱ ከተደረጉት ድርጅቶች ውጭ ያሉ በሌላ ሕግ ማለትም በንግድ ሕግ፣ በገቢ ግብር አዋጅ፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ የተሰማራ ማለስብ/ድርጅት ሪፖርት አቅራቢ አካል ይባላል።

ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ድርጅቶች፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች እና ጥቃቅን ድርጅቶች በሚል የሚለዩ ሲሆን የመለያ መስፈርት የማውጣት ሥልጣን ለቦርዱ ተሰጥቶታል። ይህ የቦርዱ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ ተቋማት ከተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ አንፃር እና በባሕሪያቸው ምክንያት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ተብለው በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲቀመጡ ተደርጓል። ከእነዚህም ውስጥ ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይገኙበታል።

ጥቃቅን ድርጅቶች ለቦርዱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ የማይኖርባቸው ሲሆን የተቀሩት ሁለቱ (የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ድርጅቶች እና አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች) ግን ቦርዱ የሚያወጣቸውን ዓለም አቀፍ የሒሳብ አያያዝ ደረጃዎች የመተግበር ግዴታ ማለትም ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫቸውን ሲያዘጋጁ እንዲሁም መግለጫዎቹን ኦዲት ሲያስደርጉ እንደ አማባበኑ ቦርዱ ያወጣቸውን ወይም የሚያወጣቸውን የሒሳብ አያያዝ የኦዲት አሰራር ደረጃዎችን መከተል ይገባቸዋል ማለት ነው። ይህንን ተላልፎ የተገኘ ሪፖርት አቅራቢ አካል ወይንም ዳይሬክተር በቦርዱ አስተዳደራዊ ኦርምጃ የሚወሰድበት ሲሆን በተጨማሪም የወንጀል ኃላፊነት ይኖርበታል።

ቦርዱ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ ሁለተኛው የሒሳብ ባለሙያዎች እና የኦዲት ባለሙያዎች የሚመለከተው ነው። ከባለሙያዎች ጋር በተያያዘ ቦርዱ የሒሳብ እና የኦዲት አገልግሎት ፍቃድ የመስጠት፣ የማደስ እና የመሰረዝ፤ ለሂሳብ/ለኦዲት ባለሙያዎች የፈተና እና የብቃት መስፈርት መመሪያ የማውጣት፤ የሒሳብ እና የኦዲት ባለሙያዎች የሚመሩበት የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ የማውጣት፣ ለባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ/ማነልበያ ሥልጠና የመስጠት ወይም ሥልጠና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች የማመቻቸት፣ የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት በሥራ ላይ የማዋል፤ የኦዲተሮችን የሥራ ጥራት የመመርመር ወይም እንዲመረመር የማድረግ፣ በባለሙያዎች እና በድንበኞቻቸው መካከል የሚፈጠር አለመግባባት በሰርቻ የሚፈታበትን መንገድ የማመቻቸት፣ በራሱ አነሳሽነት ወይም በሚቀርብ ጥቆማ መሠረት በባለሙያዎች ላይ ምርመራ የማከናወን፤ የዲሲፕሊን አርምጃ የመውሰድ፤ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የሒሳብ እና የኦዲት ሥራ ሙያን የመወከል ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ቦርዱ ከተሰጠው ተግባር ውስጥ ሦስተኛው የሒሳብ ሙያ ማኅበራትን የሚመለከት ነው። ከሒሳብ ሙያ ማኅበራት ጋር በተያያዘ ቦርዱ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ስተቋቋመ የሒሳብ ሙያ ማኅበራት ዕውቅና የመስጠት፤ የመሰረዝ እና የሒሳብ ሙያ ማኅበራትን በበላይነት የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ቦርዱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን (IFRS) በኢትዮጵያ ውስጥ ለማስተግበር እና ትግበራውን ለማስተጓጎል በተለያዩ የህገራቱ ክፍሎች በመዘዋወር የሚገዘቢ ማስጨበጫ ሥራዎች የከናወነ ሲሆን ከሚመለከታቸው የሪፖርት አቅራቢ አካላት ጋር በተለያየ ጊዜ ውይይት አድርጓል።

ቦርዱ በአሁን ሰዓት ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሚያቀርቡትን አዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት መዘጋጀታቸውን የሚመረምሩ እና የአዲት ባለሙያዎችን የሥራ ጥራት የሚገመግሙ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ አያሰራ ይገኛል። በዓለም አቀፍ ደረጃም አውቅናን አያገኘ ነው። በቦርዱ የአማካሪ ኮሚቴ ውስጥ የሚገኝ አንድ ባለሙያም በአፍሪካ ደረጃ የሒሳብ ባለሙያዎችን የሚያሰባስበው የጋን አፍሪካን የሒሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን (Pan-African Federation of Accountants, PAFA) ውስጥ ኢትዮጵያን ወክሎ በቦርዱ ስም ይገኛል። ይህም ቦርዱ በ2015 ዓም ካከናወናቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው ነው።